# የመጽሐፍ ቅዱስ

# ጂኦግራፊና

## ታሪካዊ ጥናት ምርመራ

# መቅድም

ዛሬ በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች የክርስትናን አመጣጥ ፤ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ጊዜና ምክንያት ፤ ከዚያም አለፍ ብለው ሰው የነበረበትን ሁኔታ እስከ መጀመሪያው ሰው ፣ አዳም መጀመሪያና መጨረሻ ድረስ ከመጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው ሊረዱ ይችላሉ ። ከመጽሐፍ ቅዱስ የተሻለ መጽሐፍ የለም ፤ አይኖርምም ። መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ስለ ሰው ሕይወት የዘላለም ደኅንነትና ሰፊ የክርስትና ትምህርት ስለ ማስፋፋት የሚሰነዘር አሳብና የሚዘጋጅ መጽሐፍም ለዘመናችን አስፈላጊ ነው ።

ስለዚህ ባጭሩ ከዚህ በላይ የተመለከተውን መሠረተ አሳብ በመከተልና የመጽሐፍ ቅዱስ ጂኦግራፊ ያለውን ተፈላጊነት በመገንዘብ ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘውን ትምህ ርት መነሻና መድረሻ በማድረግ ፤ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ዘመናት ከተፈጸሙት ታሪካዊ ድርጊቶች አንዳንዶቹንና ከእነዚሁም ሁኔታዎች ጋር የተያያዙትን ቦታዎች ከነካርታዎቻ ቸው የሚገልጹ

የመጽሐፍ ቅዱስ

ጂኦግራፊ

ታሪካዊ ጥናት ምርመራ

በሚል ጠቅላላ ስም የተመደቡ ሦስት ተለጣጣቂ መጻሕፍት አዘጋጅተናል ።

በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት ካርታዎች አስፈላጊ መግለጫዎች ናቸውና አንባ ቢው በሚገባ እንዲጠቀምባቸው ተስፋ እናደርጋለን ።

<u>ለአንባቢዎች ማስገንዘቢያ</u>

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ቀናት ሁሉ
እንደ አውሮፓ አቆጣጠር መሆኑን እንገልጻለን ።

## ማውጫ


ገጽ

**የብሉይ ኪዳን ክፍል።**

- የብሉይ ኪዳን ጊዜ የታወቀው ዓለም 3
- የብሉይ ኪዳን ዘመን፤ የኖኅ ዘሮች 9
- የፍልስጥኤም (ፓሌስቲን) አገር አቀማመጥ 9
- የአብርሃምና የያዕቆብ ጉዞዎች 13
- የእሥራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ ዙረት 15
- ፍልስጥኤምን በውጊያ መያዝ 17
- ሳኦል፤ ዳዊትና ሰሎሞን 19
- የሰሎሞን መንግሥት መከፋፈል 23
- የምርኮ ዘመን 23
- የአሕዛብ የምሥራቅ መንግሥታት 25
- የሮማ መንግሥት 26

**ከአራት ወንጌላት ክፍል።**

- የፍልስጥኤም (የፓለስቲን) ክፍለ ሐገሮች 28
- ኢየሩሳሌም 30
- የክርስቶስ ሕይወት
  1. የተዘጋጀበት ክፍለ ጊዜ 34
  2. ተግባሩን የጀመረበት ክፍለ ጊዜ 36
  3. የመጀመሪያውን የገሊላ ስብከት ያደረገበት ክፍለ ጊዜ 38
  4. ሁለተኛውን የገሊላ ስብከት ያደረገበት ክፍለ ጊዜ 40
  5. በአሕዛብ ወገኖች ዘንድ 42
  6. በይሁዳ የሰበከበት ክፍለ ጊዜ 44
  7. የዮርዳኖስ ማዶ (ፌርያ) ስብከት ክፍለ ጊዜ 46
  8. የሥቃይ ክፍለ ጊዜ 48
  9. የትንሣኤ ክፍለ ጊዜ 49

**ከሐዋርያት ሥራ እስከ የዮሐንስ ራእይ ክፍል**

- የወንጌል መስፋፋት 51
- የጳውሎስ ጉዞዎች 53
  1. የትንሹ እስያ አውራጃዎች 53
  2. የመጀመሪያው የጳውሎስ የስብከት ጉዞ 55
  3. ሁለተኛው የጳውሎስ የስብከት ጉዞ 57
  4. ሦስተኛው የጳውሎስ የስብከት ጉዞ 59
  - የጳውሎስ በእስረኛነት ወደ ሮም መሄድ 62

**ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት 63**

# የብሉይ ኪዳን ክፍል ።

## መግቢያ ።

መጽሐፍ ቅዱስ የጥንት መጽሐፍ ሲሆን የመጨረሻ ውም ክፍል ከተጻፈ በግምት ሁለት ሺ ዓመታት ያህል አልፈዋል ። እርሱም የታሪክ ፣ የጂኦግራፊ ፣ የትንቢት ፣ የቅኔ ፣ የሃይማኖት ትምህርት ፣ «የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን» የሚሰጥ መጽሐፍ ነው ።

# በብሉይ ኪዳን ጊዜ የታወቀው ዓለም ።

(በ፩ኛው ካርታ ላይ ተመልከቱ ።)

በብሉይ ኪዳን ጊዜ የታወቀው ዓለም ከዓባይ ወንዝ መጨረሻ (አፍ) ያሉትን ባሕሮችንና አገሮችን ይዞ እስከ ፋርስ ባሕር እራስጌ ድረስ ከዚያም በደቡብ የሲና ተራራ ፣ በሰሜን በኩል ደግሞ እስከ አራራት ተራራዎች ያሉትን ይጠቀልላል ። እርሱም የኢትዮጵያን ስፋት ከሁለት እጥፍ የሚበልጥ በግምት ከዚሁ መሬት ሁለት ሦስተኛው እጅ ሰው የማይኖርበት በረሃ ነው ።

## ስለ ባሕሮች ፣ የተራራ ሰንሰለት ፣ ወንዞች ፣ አገሮችም ።

### ባሕሮች ።

፩ኛ በብሉይ ኪዳን የዓለም ካርታ ውስጥ በስተ ሰሜን ምሥራቅ ጠረፍ በኩል ዙሪያውን በምድር የተከበበ ከሁሉ የበለጠ ስፋት ያለው ውኃ የካስፒያን ባሕር ይገኛል ።

፪ኛ በደቡባዊ ምሥራቅ ወሰን በኩል በብሉይ ኪዳን ታሪክ የተጠቀሱት የኤፍራጥስና የጤግርስ ወንዞች የሚፈሱበት የፋርስ ባሕር ይገኛል ።

፫ኛ ሁለቱ የባሕር ሰላጤዎች በኤርትራ ባሕር ሰሜናዊ በኩል የሚገኙ የስዌዝ ባሕርና የአካባ ባሕር በካርታው በስተ ደቡብ ምዕራብ በኩል ይገኛሉ ።

፬ኛ የሜዲቴራኒያ ባሕር ወይም ታላቁ ባሕር የምዕራባዊውን ወሰን ይይዛል ።

፭ኛ በከነዓን ያለው የጨው ባሕር ከታላቁ ባሕር 400 ሜትር ዝቅ ያለ ነው ።

### የተራራ ሰንሰለት ።

፩ኛ የአራራት ተራራዎች በካስፒያን ባሕርና በትንሹ እስያ መካከል ይገኛሉ ። ከሁሉ የበለጠው የተራራ ጫፍ 5,500 ሜትር ነው ።

፪ኛ የካስፒየን ተራራዎች ከአራራት ወጥተው የካስፒየንን ባሕር ከደቡብ ዳር ጀምረው እስከ ምሥራቃዊው ጠረፍ ይከቡታል ።

፫ኛ የዛግሮስ ተራራዎች ደግሞ ከአራራት ተነሥተው ወደ ደቡባዊ ምሥራቅ አቅጣጫ ወደ ፋርስ ባሕር ሰሜናዊ ጠረፍ ይደርሳሉ ።

፬ኛ የሊባኖስ ተራራ ሰንሰለት ከአራራት ተራራ ሰንሰለት ከምዕራብ ጐን ተነሥቶ በታላቁ ባሕር ጠረፍ አቅራቢያ አድርጎ በስተ ደቡባዊ አቅጣጫ ይጓዛል ።

## ወንዞች ።

፩ኛ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከታወቁ ወንዞች የኤፍራጥስ ወንዝ በስፋትና በርዝመት ከፍ ያለ ነበር ። የዚህም ወንዝ መነሻዎች በአራራት (በአርመን) አገር ሲሆኑ ርዝመቱም 2,840 ኪሎሜትር ነው ። ከርዝመቱ ግማሽ የሚበልጠውን ርቀት በጀልባ ወደ ላይ ያስኬዳል ፤ ከባቢሎን ከተማ ሲደርስ ስፋቱ አንድ ኪሎሜትር ተኩል ይሆናል ።

፪ኛ ጤግሮስ በመጽሐፍ ቅዱስ ሒዴቄል የተባለው ወንዝ ከአራራት ሸንተረር ይነማና በስተ ደቡባዊ ምሥራቅ አቅጣጫ ይወርድና ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ይገባል ። ርዝመቱም 1,830 ኪሎሜትር ይሆናል ።

፫ኛ የዮርዳኖስ ወንዝ ከሁሉ ያነሠ ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉ የታወቀ ነው ። እርሱም ከአርሞንዔም ተራራ ሥር ተነሥቶ ወደ ጨው ባሕር ይወርዳል ። (ስለ ዮርዳኖስ ወንዝ በተጨማሪ በዚሁ መጽሐፍ በገጽ ፲፩ በሰፌው እንማራለን ።)


## አገሮች ሁናቴ ።

### ፩ኛ በተራራው መካከል ያሉ አገሮች —

ሀ) የአርመን አገር ፤ ይህ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ባይገኝም ፤ ትርጉሙ የመነጨው ከአራራት ቃል ነው ። ይህም አገር በካስፒየን ባሕር በስተ ምዕራብ ይገኛል ።

ለ) ሚዶን ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ 633 ዓመታት በፊት ሚዶን የተባለ መንግሥት ተቋቋመ ። ለትንሽ ጊዜ ብቻ አይሎ በ550 ዓመተ ዓለም ወደቀ ፤ ትልቅነቱም ወደ ፋርስ ዞረ ። (የሚከተለውን ማስታወሻ ተመልከቱ

ሐ) ፋርስ ፤ በቀድሞ ጊዜ በሚዶን መንግሥት ሥር ነበር ። ነገር ግን በቂሮስ የተመሩት የፋርስ ሕዝብ አምፀው ሚዶንን አሸነፉ ፤ በመጨረሻውም በ538 ዓመተ ዓለም ባቢሎንን ተዋግተው ያዙት ። (ኢሳ. ፵፭ ፥ ፩ ና ፪ ፤ ፵፬ ፥ ፳፰ ፤ ፵፭ ፥ ፩ ተመልከቱ ።) የፋርስ መንግሥት ግዛት ከምሥራቃዊ ከአሕዛብ መንግሥታት ሁሉ ከፍ ያለ ሲሆን እስከ ኢትዮጵያ ጠረፍና እስከ ህንድም ድረስ ተስፋፍቶ ነበር ።




፩ኛ ካርታ
በብሉይ ኪዳን ጊዜ
የታወቀው ዓለም

፱ኛ የቆላ (ዝቅ ያሉ) አገሮች—

ሀ) አሶር ፤ እርሱም ከፋርስ ባሕር በስተ ሰሜን ይገኛል ። ዋናው ከተማው ነነዌ ነበር ።

ለ) ዒላም ፤ ይህ አገር ከአሶር በስተ ደቡብ ምሥራቅና ከፋርስ በስተ ምዕራብ በዛግሮስ ተራራዎችና በጤግሮስ ወንዝ መካከል የሚገኝ ነው ። ይህም አገር በአሶር መንግሥት ሥር ወደቀ ።

ሐ) ሜሶፖታሚያ (በሁለት ወንዝ መካከል) ፤ ይህ አገር በጤግሮስና በኤፍራጥስ ወንዞች መካከል የሚገኝ ለም ሜዳ የሆነ አገር ነበር ። በኋላ ቆይቶ የአሶር ግዛት ክፍል ሆነ ።

መ) የከለዳውያን አገር ፤ ይህ አገር በቀድሞ ጊዜ ሰናዓርና ባቢሎን ይባል ነበር ። ከከተማዎቹ አንዱ ኡር የተባለ አብርሃም የተወለደበት ቦታ ነው ።

ሠ) ዓረብ ፤ የዓረብ በረሃ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከታወቀው የዓለም ካርታ ውስጥ ሰፊውን ክፍል ይዞ የሚገኝ ነው ፤ እርሱም ከፋርስ ባሕር እስከ ኤርትራ ባሕር አቋርጦ ከዚያም በስተ ሰሜን በኩል እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይደርሳል ።ሰዎች ዞሮ መጓዝን በመምረጥ በረሃውን በቀጥታ ሊያቋርጡ አይፈልጉም ነበር ።

፲ኛ በታላቁ ባሕር ጠረፍ የሚገኙ አገሮች—

ሀ) ትንሹ እስያ (አሁን ቱርክ) ፤ በብሉይ ኪዳን የሒታውያን ምድር ይባል ነበር ። ይህም አገር በአዲስ ኪዳን ታሪክ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል ።


ለ) ሶርያ ፤ ይህ በስተ ሰሜን የሚገኝ አገር በብሉይ ኪዳን ዘመን ዋና ከተማው ደማስቆ ነበር ፤ ነገር ግን በኋላ አንጾኪያ የታወቀና የበለጠ ከተማ ሆነ ።

ሐ) ፊንቄ ፤ ይህ አገር በታላቁ ባሕርና በሊባኖስ ተራራዎች መካከል የሚገኝ የሁለቱ ታላላቅ ከተማዎች የጢሮስና የሲዶና አገር ነበር ።

መ) ፍልስጥኤም (ፓሌስቲን) ፤ ይህ አገር ከፊንቄ በስተ ደቡብ ከዓረብ ምድረ በዳና ከታላቁ ባሕር መካከል የሚገኝ ነው ።

ሠ) ምድረ በዳ ፤ ከፍልስጥኤም በስተ ደቡብ የሚገኝ እስራኤላውያን አርባ ዓመታት ሲዞሩ የነበሩበት ምድረ በዳ ነው ። የሚገኘውም በዓረብ ክፍል ነው ።

ረ) ምድረ ግብፅ ፤ ይህ ምድር በአፍሪቃ በስተ ሰሜን ምሥራቅ ፤ ከኢትዮጵያ በስተ ሰሜን ምዕራብ በኩል ይገኛል ።



የአትላንቲክ ውቅያኖስ
N
፪ኛ ካርታ
የኖኅ ዘሮች
የሴም ዘሮች
የካም ዘሮች
የያፌት ዘሮች
አውሮጳ
ጥቁር ባሕር
የካስፒያን ባሕር
እስያ
ታላቁ ባሕር
ከነዓን
አ ፍ ሪ ቃ
የኤርትራ ባሕር
ዓረብ
ኩሽ
ህንድ
የህንድ ውቅያኖስ

# የጥንታዊ ዘመን ፤ የኖኅ ዘሮች ።

(በ፪ኛው ካርታ ላይ ተመልከቱ ።)

የኖኅ ሦስቱ ልጆች ያፌት ፤ ካም ፤ ሴም ነበሩ ።

**የያፌት ዘሮች ።**

የያፌት ዘሮች በዘፍጥረት ም. ፲ ፥ ቁ. ፪ «የያፌት ልጆች» የተባሉ ከሰባት ቤት ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ ሕዝቦች የህንድና የአውሮጳ ዘር ይባላሉ ፤ እነዚህም ግሪክ ፤ ጀርመን ፤ ህንድን የመሳሰሉ ናቸው ።

**የካም ዘሮች ።**

የካም ዘሮች በአራት ዋና ዋና ነገዶች ተከፋፍለዋል ። የእነዚህ ነገዶች መኖሪያቸው አብዛኛውን በአፍሪቃ ውስጥ ነው ።

**የሴም ዘሮች (ሴማውያን) ።**

የሴም ዘሮች የተባሉትን አምስቱን ትልልቅ ነገዶች የመሠረተ ሴም ነበር ። ከእነዚህም ነገዶች ሁለቱ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል —

፩ኛ ከለዳውያን ፤ አርፋክስድ (ዘፍ. ፲፩ ፥ ፲) የከለዳውያን አባት ነበር ። የሕዝቡም መኖሪያ በፋርስ ባሕር ራስጌ ነበር ። አብርሃም የመጣው ከእነዚህ ዘር ነው ።


፪ኛ ነገደ አራም ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አራም ሶርያ እየተባለ ይጠራል ። ይህ ነገድ ከከነዓን አንሥቶ በስተ ምዕራብ ወደሚገኘው እስከ ፊንቄ ፤ ከዚያም በስተ ሰሜን እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ፤ በስተ ምሥራቅ ደቡብ እስከ ትልቁ በረሃ ድረስ ያለውን ቦታ ይዞ ነበር ።

# የፍልስጥኤም (ፓሌስቲን) አገር አቀማመጥ ።

(በ፫ኛው ካርታ ላይ ተመልከቱ ።)

**ስፋቱ ።**

ፍልስጥኤምና ከነዓን የተባሉ ስሞች አንድ አይደሉም ። ከነዓን በዮርዳኖስና በታላቁ ባሕር መካከል ያለውን ምድር ያመለክታል ። ሰሜናዊው ወሰኑም የሊባኖስ ተራራ ሲሆን ደቡባዊው ወሰኑ ደግሞ በረሃው ነው ። ነገር ግን ፍልስጥኤም ሲባል ከነዓንን ብቻ ሳይሆን ከዮርዳኖስ ማዶ ምሥራቅ ያለውንም ክፍለ አገር ይይዛል ። ይኸውም በሰሜን በሊባኖስ ተራራ ፤ በምሥራቅ በዓረብ ምድረ በዳና በደቡብ በሲና ሰላጤ የተከበበ ፤ በምዕራብ በኩል ከታላቁ ባሕር ተዋስኖ ስፋቱ በግምት 30,000 ኪሎሜትር ካሬ የሆነ አገር ነው ።


፫ኛ ካርታ
ፍልስጥኤም
(ፓሌስቲን)
N
የአርሞንዔም ተራራ
የሜሮም ውኃ
ፊንቄ
ገሊላ
የገሊላ ባሕር
የቀርሜሎስ ተራራ
የይዝሬኤል ሜዳ
ደብረ ታቦር
ታላቁ ባሕር
ሣሮን
የገልዓድ ተራራ
የጊልቦዓም ተራራ
የዔባል ተራራ
ሰማርያ
የዮርዳኖስ ወንዝ
የፍልስጥኤማውያን አገር
ኢየሩሳሌም
ይሁዳ
የዓረብ ምድረ በዳ
የጨው ባሕር
ተራራዎች
ነገብ
0 10 20 30 40 50
ኪሎሜትር

የተፈጥሮ አከፋፈል ።

፩ኛ የባሕር ጠረፍ ፤ ቆላማ ሜዳ ። በታላቁ ባሕር ጠረፍ አግድም ከላይ እስከ ታች የተዘረጋው መሬት ለጥ ያለ ሜዳ ነው ። በመካከሉ ላይ ብቻ የቀርሜሎስ ተራራ ከፍታው ሜዳውን ያቋርጣል ። ከዚህ ተራራ በስተ ሰሜን የሚገኘው መሬት ጠባብ ነው ፤ ነገር ግን ከተራራው በስተ ደቡብ የሚገኘው ስፋቱ 13 ኪሎሜትር ሲሆን በመጨረሻውም በደቡባዊው ጠረፍ ላይ ያለው ስፋት እስከ 32 ኪሎሜትር ይደርሳል ። ሜዳው በሞላ በጣም ለምለም ነው ፤ ከባሕር ከፍታውም ከ30 እስከ 60 ሜትር ድረስ ይደርሳል ። በዚህ ስፍራ በብሉይ ኪዳን ዘመን ጥቂት እስራኤላውያን ብቻ ይገኙበት ነበር ። አብዛኞዎቹም ደጋ ደጋውን ይዘው ይኖሩበት ነበር ። ሜዳውም በአራት ክፍሎች ይከፈላል —

ሀ) ፊንቄ ። ይህ ከቀርሜሎስ ተራራ በስተ ሰሜን የሚገኝ አገር ነው ።

ለ) ሣሮን ። ይህም የሚገኘው ከቀርሜሎስ ተራራ በስተ ደቡብ ነው ።

ሐ) የይዝሬኤል ሜዳ ።

መ) የፍልስጥኤማውያን ምድር ። ፍልስጥኤማውያን የተባሉ የእስራኤሎች የጥንት ጠላቶች ይኖሩበት የነበረው ከሣሮን በስተ ደቡብ የሚገኝ አገር ነው ። ከዚሁ ሕዝብ በተወረሰ ስም አገሩም በጠቅላላው ፍልስጥኤም ተብሎ ተጠራ ።

፪ኛ ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ተራራማ ክፍል ። በታላቁ ባሕር ጠረፍ በሚገኘው ስፍራ በቆላማ ሜዳና በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ያለው ስፍራ ተራራማ ነው ። በዚሁም ተራራ ሸንተረር ላይ የእስራኤል ሕዝቦች ዋናው መኖሪያቸው ነበር ። ይህም የአገር ክፍል አቀማመጥና የተፈጥሮ አኳኋን ሲታይ በአምስት

ሀ) ከፍተኛው ገሊላ ። (በግምት ከተራራ ሁሉ ከፍታው 860 ሜትር

ለ) ዝቅተኛው ገሊላ ። (በግምት ከተራራ ሁሉ ከፍታው 560 ሜትር

ሐ) የሰማርያና የይሁዳ ተራራማ አገሮች ። እነዚህ አገሮች በብሉይ ኪዳን ሲጠቀሱ «የኤፍሬም ተራራ» እና «የይሁዳ ተራራ» ይባላሉ ። በግምት የተራራዎቹ ከፍታ ከ600 እስከ 900 ሜትር ይደርሳል ።

መ) ዝቅተኞቹ ኰረብታዎች ደግሞ በተራራዎቹ ጥግ ጥጉን የሚገኙ ከባሕር ጠለል እስከ 150 ሜትር ከፍ ይላሉ ።

ሠ) ነገብ ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የደቡብ ምድር ወይም የአዜብ ምድር እየተባለ የሚጠራው ነው ። ትርጉሙም ደረቅ ማለት ነው ።

፫ኛ የዮርዳኖስ ሸለቆ ። ይህ ሸለቆ መነሻው ከአርሞንዔም ተራራ ሲሆን መድረሻውም የጨው ባሕር ነው ፤ ከፍታውም እያዘቀዘቀ ይሄዳል ። እርሱም የዮርዳ

ኖስ ወንዝ እምንጩ ላይ ከባሕር ከፍታው 500 ሜትር ሲሆን በመጨረሻውም በጨው ባሕር አጠገብ ከባሕር ጠለል 400 ሜትር ዝቅ ይላል ። ወደ ሰሜን ከፍ ብሎ ከግራውና ከቀኙ የአርሞንዔምና የሊባኖስ ተራራዎች ይገኙበታል ።

<u>የዮርዳኖስ ወንዝ ።</u> ይህ ወንዝ በዮርዳኖስ ሸለቆ በኩል ይወርዳል ። እርሱም ከአርሞንዔም ተራራ ተነሥቶ በደቡብ በሜሮም ውኃ በኩል አድርጎ ወደ ገሊላ ባሕር ይገባል ። ከገሊላ ባሕር ተነሥቶ 100 ኪሎሜትር ርዝመት ባለው ገደልማ የወንዝ ሸለቆ በኩል አልፎ በጨው ባሕር ውስጥ ይገባል ። ጠቅላላው የወንዙ ርዝመት 320 ኪሎሜትር ሲሆን የወንዙ ጐን ስፋት በ25 ና በ50 ሜትር መካከል በየቦታው የተለያየ ነው ። በጉዞው መጨረሻ ሲታይ ከምንጩ 900 ሜትር ያህል ዝቅ ብሎ ይገኛል ።


<u>ሦስቱ ሐይቆች ።</u> እነዚህም ሐይቆች የሚገኙ በዮርዳኖስ ሸለቆ ውስጥ ነው ።

ሀ) <u>የሜሮም ውኃ ።</u> ስፋቱ 5 ኪሎሜትር ነው ። የሚገኘውም በሰሜናዊ ገሊላ ነው ።

ለ) <u>የገሊላ ባሕር ።</u> ርዝመቱ 24 ኪሎሜትር ሲሆን ጐኑ 16 ኪሎሜትር ነው ።

ሐ) <u>የጨው ባሕር ።</u> አቀማመጡ በዮርዳኖስ ሸለቆ በስተ ደቡብ ጫፍ ነው ። ርዝመቱ 72 ኪሎሜትር ሲሆን ጥልቀቱ አንዳንድ ቦታ ላይ እስከ 800 ሜትር ይደርሳል ። ከዚህ በፊት እንደተማርነው ከታላቁ ባሕር ዝቅታው 400 ሜትር ነው ።

## <u>የፍልስጥኤም ተራራዎች ።</u>




**የፍልስጥኤም ተራራዎች**

(ይህንን ክፍል ስታነቡ ከላይ የሚገኘውን ሥዕል እየተመለከታችሁ አጥኑ ።)

1. <u>የአርሞንዔም ተራራ ።</u>

ይህ ተራራ የእስራኤል ሰሜናዊ ወሰን ክልል ነው ። እርሱም ክርስቶስ ወደ ብሩህነት የተለወጠበት ተራራ ይሆናል ።

2. <u>የሊባኖስ ተራራ ።</u>

በዚህ ተራራ ላይ ታላቅ የጥድ ዛፍ ደን ነበር ። በኢየሩሳሌም ውስጥ ለተሠራው ለቤተ መቅደሱ የሚሆን እንጨት የተወሰደው ከዚሁ ተራራ ደን ነው ።

3. <u>የዔባል ተራራ ።</u>

ሙሴ እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን አገር ከመግባታቸው በፊት በዚሁ ተራራ ላይ እንደደረሱ የእግዚአብሔርን መሠውያ እንዲሠሩና ቃላተ ኦሪቱን በድንጋዮች ላይ እንዲጽፉ አዘዛቸው ።

4. <u>ደብረ ዘይት ።</u>

ይህ ተራራ የሚገኘው በኢየሩሳሌም አጠገብ ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተያዘው በዚሁ ተራራ ላይ ነበር ።

5. <u>የገልዓድ ተራራ ።</u>

ያዕቆብና ላባን የሰላም ኪዳን የተስማሙትና ለኪዳኑም ምልክት የድንጋይ ካብ ያቆሙት እዚሁ ተራራ ላይ ነበር ።

6. <u>ደብረ ታቦር ።</u>

ሲሣራን ያሸነፈው የባርቅ ጦር ሠራዊት የተሰበሰበው እዚህ ተራራ ላይ ነበር ።

7. <u>የቀርሜሎስ ተራራ ።</u>

ኤልያስ ያቀረበውን መሥዋዕት እንዲበላለት ከሰማይ እሳት ያወረደውና የበዔልን ነቢያት ከንቱ መሆናቸውን ያሳፈራቸው እዚህ ተራራ ላይ ነበር ።

8. <u>የጊልቦዓ ተራራ ።</u>

የፍልስጥኤም ሰዎች የእስራኤልን ሰዎች ድል ያደረጉበትና ሳኦልና ዮናታን የተገደሉበት ቦታ እዚህ ነበር ።

# የአብርሃምና የያዕቆብ ጉዞዎች ።

በኦሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ ፲፩ መጨረሻ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ስለጠቅላላው የሰው ፍጥረት መቀጠሉ ቀርቶ ስለ አንድ ሰው ቤተ ሰብ ታሪክ መዘርዘር ይጀምራል ። ይኸውም የአብርሃም ቤተ ሰብ ነው ።

## የአብርሃም ጉዞዎች (በጉዞውም ላይ የደረሰ ታሪክ) ።

፩ኛ ከኡር እስከ ካራን ። (ዘፍ. ፲፩ ፥ ፳፯—፴፪)
ኡር የተባለው ከተማ በከለዳውያን አገር በኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ደቡብ ሲሆ
ን ፤ ካራን በሜሶፖታሚያ አገር የሚገኝ ነበር ። የአብርሃም ቤተ ሰብ ኡርን
ለቅቆ አባቱ ታራ እስኪሞት ድረስ በካራን ተቀመጠ ።

፪ኛ ወደ ምድረ ግብፅ (ምስር) መውረድ ። (ዘፍ. ፲፪ ፥ ፲— ፳)
አብርሃም ከግብፅ ወደ ቤቴል ተመለሰ (ዘፍ. ፲፫ ፥ ፩—፬) ።

፫ኛ ወደ ኬብሮን መሄድ ። (ዘፍ. ፲፫ ፥ ፭—፲፰)

፬ኛ የሰዶምና ገሞራ ከተማዎች መጥፋት ። (ዘፍ. ምዕ. ፲፰ እስከ ምዕ. ፲፱ ፥ ፳፱)
እነዚህ ከተማዎች በዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ በጨው ባሕር አጠገብ የነበሩ ይመ
ስላል ። ዛሬ ግን የከተማዎቹ ስፍራ ወዴት እንደሆነ አይታወቅም ።

፭ኛ በቤርሳባዕ መቀመጥ ። (ዘፍ. ምዕ. ፳ እስከ ምዕ. ፳፩ ፥ ፲)

**፮ኛ ለመሥዋዕት ይስሐቅን ማቅረብ ። (ዘፍ. ምዕ. ፳፪)**
**ይህም የሆነው በኢየሩሳሌም በሞርያ ተራራ ላይ ነበረ ። ከዚህ ጊዜ በኋላ አንድ ሺ ዓመታት ገደማ ቆይቶ ልክ በዚሁ ስፍራ ላይ ለእግዚአብሔር መቅደስ ተሠራ ።**

**፯ኛ አብርሃምና ሣራ ሲሞቱ በኬብሮን በመክፈላ ዋሻ ተቀበሩ ።**

## የያዕቆብ ጉዞዎች (በጉዞውም ላይ የደረሰ ታሪክ) ።

፩ኛ ከቤርሳባዕ እስከ ካራን መሸሽ ። (ዘፍ. ፳፰ ፥ ፲ እስከ ምዕ. ፴)
ያዕቆብ ከአባቱ ቤት ወደ ካራን ሲሸሽ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን 16 ኪሎ
ሜትር ርቆ በሚገኘው ቤቴል በተባለ ስፍራ ከሰማይ እስከ መሬት መሰላል
ተዘርግቶ በጫፉም ላይ እግዚአብሔር ቆሞ ራእይ አየ ፡ ካራን ከአገሩ ከቤርሰ
ባዕ 720 ኪሎሜትር ይርቅ ነበር ። እርሱም በካራን ሃያ ዓመታት ቆየ ።

፪ኛ ወደ ከነዓን መመለስ ። (ዘፍ. ምዕ. ፴፩ እስከ ምዕ. ፴፫)

፫ኛ በከነዓን መቀመጥ ። (ዘፍ. ምዕ. ፴፬ ና ፴፭ ፤ ምዕ. ፴፯ እስከ ምዕ. ፵፭)
በቤተ ልሔም አጠገብ ሚስቱ ራሔል ስለሞተችበት እዚያው ተቀበረች
(ዘፍ. ፴፭ ፥ ፲፯—፳) ። የሸመገለውን አባቱን በኬብሮን ተገናኘው
(ዘፍ. ፴፭ ፥ ፳፯) ፤ እዚህም ተቀምጦ ሳለ ልጁ ዮሴፍ እንደ ባርያ ተሸጠበት ።

፬ኛ ወደ ምድረ ግብፅ መውረድ ። (ዘፍ. ምዕ. ፵፮ እስከ ምዕ. ፵፱)
እዚህ የያዕቆብ ቤተ ሰብ 430 ዓመታት ያህል ተቀመጠ (ዘፀ. ፲፪ ፥ ፵) ።

፳፫ የያዕቆብ ሞት ። (ዘፍ. ፶ ፥ ፩—፲፬)
የያዕቆብ አስከሬን ከምድረ ግብፅ ተወስዶ ወገኖቹ በተቀበሩበት በኬብሮን ምድር ተቀበረ ።

# የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ ዙረት ።

(1270 እስከ 1230 ዓመተ ዓለም) (በ፬ኛው ካርታ ላይ ተመልከቱ ።)

፩ኛው ጉዞ ፤ ከረዕምሴስ እስከ ኤርትራ ባሕር ። (ዘፀ. ምዕ. ፲፪ እስከ ምዕ. ፲፭ ፥ ፳፩ ፤ ዘኁ. ፴፫ ፥ ፩—፰)

፪ኛው ጉዞ ፤ ከኤርትራ ባሕር እስከ ሲና ተራራ ። (ዘፀ. ፲፭ ፥ ፳፪ እስከ ምዕ. ፲፱ ፥ ፪ ፤ ዘኁ. ፴፫ ፥ ፰—፲፭)
በዚሁም ጉዞ ላይ እስራኤላውያን ያረፉባቸው ስፍራዎች የሚከተሉት ናቸው—

ሀ) ማራ ። በዚህም ስፍራ መራራ የነበረ ምንጭ ወደ ጣፋጭነት ተለወጠ ።

ለ) ኤሊም ።

ሐ) የሲን ምድረ በዳ ። የእስራኤል ልጆች እዚህ ሲደርሱ ምግብ በማጣት ፈተና ላይ ወደቁ ። እግዚአብሔርም እንጀራ (መና) ይመግባቸው ጀመር (ዘፀ. ምዕ. ፲፮) ።

መ) ረፊዲም ። በዚህ ስፍራ ሙሴ ድንጋዩን መትቶ ውኃ አፈለቀላቸው (ዘፀ. ፲፯ ፥ ፩—፯) ። እዚህ ደግሞ እስራኤሎች የመጀመሪያውን ጦርነት አደረጉ ፤ ይኸውም ከዓማሌቃውያን ጋር ነበር (ዘፀ. ፲፯ ፥ ፰—፲፮) ። በዚህ ጦርነት ጊዜ የሠራዊቱ መሪ የነበረው ኢያሱ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተጠቀሰ እናያለን ። ከባርነት ነፃ ከወጡበት ከግብፅ አገር እስከ ረፊዲም ድረስ ጉዞው ሁለት ወር ተኩል ያህል ፈጀ ።


ረ) የሲና ተራራ ። በዚህ ተራራ በቆዩበት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያደረጉአቸው ዋና ዋና ነገሮች እንደሚከተሉት ናቸው—

፩ኛ ሕግን ተቀበሉ (ዘፀ. ምዕ. ፲፱ እስከ ምዕ. ፴፩ ፤ ምዕ. ፴፬) ።

፪ኛ የወርቅ ጥጃ ጣዖት ሠርተው ሰገዱለት (ዘፀ. ምዕ. ፴፪ ና ፴፫) ።

፫ኛ «የእግዚአብሔርን ማደሪያ» ሠሩ (ዘፀ. ምዕ. ፴፭ እስከ ምዕ. ፵) ።

፫ኛው ጉዞ ፤ ከሲና ተራራ እስከ ቃዴስ በርኔዓ ።
በዚሁም ጉዞ ላይ ሐሴሮት በሚባል ሠፈር ሚሪያም አሮንን በማባበል በሙሴ ላይ አመፀች ። እግዚአብሔርም በለምጽ ቀጣት ፤ ግን በሙሴ ጸሎት ተፈወሰች (ዘኁ. ምዕ. ፲፪) ።
በቃዴስ በርኔዓ አሥራ ሁለት ሰላዮች ወደ ከነዓን አገር ተልከው ከካሌብና



ታላቁ ባሕር
ከነዓን
የኔቦ ተራራ
የጨው ባሕር
ግብፅ
ረዕምሴስ
ጎሼን
ቃዴስ በርኔዓ
የሆር ተራራ
ኤላት
ማራ
ኤሊም
ሐሴሮት
ረፊዲም
የሲና ተራራ
የሲን ምድረ በዳ
N
0 20 40 60 80 100
ኪሎሜትር
፩ኛ ካርታ
የእስራኤል ሕዝብ
በምድረ በዳ ዞረት
የኤርትራ ባሕር

ከኢያሱ በስተቀር ሌሎቹ ሁሉ ተስፋ የሚያስቀርጥ ወሬ አመጡ ። ስለዚህም ያ ትውልድ (በእግዚአብሔር ያልተማመኑቱ) ተስፋ ወደ ተሰጣቸው ምድር ሊገቡ አልተፈቀደላቸውም (ዘኍ. ምዕ. ፲፫ ና ፲፬) ።

<u>፬ኛ ና ፭ኛ እንዲሁም ፮ኛው ጉዞዎች ፤</u> ከቃዴስ በርኔ እስከ ሆር ተራራ ፤ ከዚያም እስከ ኤላት (ዔጽዮን ጋብር) ፤ ከኤላት ወደ ቃዴስ በርኔ መመለስ ።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው አሮን በጉዞአቸው መጨረሻ ግድም በሆር ተራራ ሞተ (ዘኍ. ፳ ፥ ፳፪—፳፱ ተመልከቱ) ።

በቃዴስ በርኔ የሆነ ታሪክ—ድንጋዩ ውኃ እንዲሰጥ ሙሴ ባለማመንና እግዚአብሔርንም ባለመቀደስ ስለመታው ወደ ከነዓን እንዳይገባ ተከለከለ (ዘኍ. ፳ ፥ ፩—፲፫) ።

<u>፮ኛው ጉዞ ፤</u> ከቃዴስ በርኔ እስከ ኤላት እንደገና መሄድ ።

<u>፯ኛው ጉዞ ፤</u> ከኤላት እሰከ ዮርዳኖስ ።

በዚህ ጉዞ ላይ ሳሉ ሕዝቡ በመርዘኛ እባብ እየተነደፉ በታመሙ ጊዜ እንዲድኑ ሙሴ የናስ እባብ ሰቀለላቸው (ዘኍ. ፳፩ ፥ ፬—፱) ።
በዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ጠረፍ የሆነ ታሪክ—

ሀ) በለዓም ትንቢት እንደተነገረ (ዘኍ. ምዕ. ፳፪ እስከ ምዕ. ፳፬) ።

ለ) ለሮቤል ፤ ለጋድና ለእኩሌታው የምናሴ ነገድ ርስት እንደተሰጠ (ዘኍ. ምዕ. ፴፪) ።

ሐ) ሙሴ ወደ ኔቦ ተራራ ወጥቶ ተስፋ የተሰጠውን አገር በሩቁ አይቶ እንደ ሞተ (ዘዳ. ምዕ. ፴፬) ።

# <u>ፍልስጥኤምን በውጊያ መያዝ ።</u>

(ስለ ነገዶች ርስት መከፋፈል በ፫ኛው ካርታ ላይ ተመልከቱ ።)


የእስራኤል ልጆች አርባ ዓመታት በምድረ በዳ ከዞሩ በኋላ ሰባት ዓመት ደግሞ ባለማቋረጥ ተዋጉ ። አገሩን ለመያዝ ያደረጉአቸው ልዩ ልዩ ውጊያዎች የሚከተሉት ናቸው—

<u>የምሥራቃዊ ፍልስጥኤምን አገር ድል ማድረግ ።</u>

፩ኛ ጊልዓድን ድል ማድረግ (ዘኍ. ፳፩ ፥ ፳፩—፴፩) ።

፪ኛ ባሳንን ድል ማድረግ (ዘኍ. ፳፩ ፥ ፴፪—፴፭) ።

፫ኛ ምድያንን ድል ማድረግ (ዘኍ. ምዕ. ፴፩) ።




፫ኛ ካርታ
የፍልስጥኤም አገር
በእስራኤል ነገዶች
እንደተከፋፈለ

የምዕራባዊ ፍልስጥኤምን አገር ድል ማድረግ ። ይህ ውጊያ ከሙሴ ሞት በኋላ ሲሆን በኢያሱ መሪነት የተደረገ ነው ።

፩ኛ የመካከለኛውን ክፍለ አገር ድል ማድረግ (ኢያ. ምዕ. ፫ እስከ ምዕ. ፱) ። የተያዙ ዋና ከተማዎች ኢያሪኮና ዓይ ነበሩ ።

፪ኛ የደቡባዊን ክፍለ አገር ድል ማድረግ (ኢያ. ምዕ. ፲) ።

አምስቱ የአሞራውያን ነገሥታት በኢያሪኮና በዓይ የነበረው ኃይለኛ ጦርነት ስለ አሰጋቸው እያየሉ የመጡባቸውን እስራኤላውያንን ለመመከት በአንድነት ተሠለፉ ። ዋናው መሪያቸው የኢየሩሳሌሙ ንጉሥ አደኒጼዴቅ ነበረ ። የእር ሱም ተባባሪዎች የኬብሮን ፤ የየርሙት ፤ የለኪሽ ፤ የዔግሎን ንጉሦች ነበሩ ። ዋናው ጦርነት የተደረገው በቤት ኮሮን ነበረ ። አምስቱ ነገሥታት ተማርከው ተገደሉ ። ቀጥሎም ሊብና ፤ ለኪሽ ፤ ዔግሎን ፤ ኬብሮንና ዴቢር የተባሉ ከተማ ዎች ተያዙ ።

፫ኛ የሰሜናዊን ክፍለ አገር ድል ማድረግ (ኢያ. ምዕ. ፲፩) ።

በስተ ሰሜን በሜሮም ውኃ አጠገብ ከሆነው ውጊያ በኋላ ዋና ዋናው ጦርነት ስለተፈጸመ አገሪቱም ከጦርነት አረፈች (ኢያ. ፲፩ ፥ ፳፫) ።


ምንም እንኳን ጠቅላላውን ጦር ድል ቢያደርጉም የአገሩን ሕዝብ የመውረርና የማጥ ፋት ተግባር ገና አላለቀም ነበር ። በዘመሳፍንት ምዕ. ፩ ፥ ፩—፰ ና በምዕ. ፲፰ ፤ እንዲ ሁም በሌሎች ቦታዎች የእስራኤል ሕዝብ ይህን ተግባር እንዴት እንዳከናወኑ እናገኛለን ።


# ሳኦል ፤ ዳዊትና ሰሎሞን ።

(በ፯ኛውና በ፰ኛው ካርታ ላይ ተመልከቱ ።)

እስራኤላውያን ተስፋ ወደ ተሰጣቸው ምድር ከገቡ በኋላ በአካባቢው የነበሩት ነገ ዶች ብዙ ያስቸግሩአቸውና ይጨቁኑአቸው ነበር ። በተጨነቁም ጊዜ ሁሉ ሕዝቡን ሊያ ድን እግዚአብሔር መሳፍንት የተባሉትን መሪዎች ያስነሣላቸው ነበር ። ቢሆንም በመ ሳፍንት መገዛትን ስላልወደዱና የረጋ መንግሥት የማቋቋም ፍላጎት ስላደረባቸው ፥ በመ ጨረሻው ንጉሥ ይሻለናል በማለት ሳኦልን አነገሡት ።

ሳኦልም ከአካባቢው ሕዝቦች ጋር ብዙ ጦርነቶች አደረገና በካርታው ላይ እንደሚ ታየው 15,000 ኪሎሜትር ካሬ የሚያህል ስፋት ያለውን አገር ጠቅልሎ ያዘ ። ከዚያ በኋላ ዳዊት ዙፋኑን ወርሶ ለልጁ ለሰሎሞን 150,000 ኪሎሜትር ካሬ ስፋት ያህል ያለ ውን አገር አወረሰው ። የሰሎሞን መንግሥት የሰላም መንግሥት ነበረ ። በእርሱ ዘመን አ ቱባ ዳዊት ለእግዚአብሔር ሊሠራው አቅዶት የነበረውን የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ሠርቶ ጨረሰ ።


የሊባኖስ ተራራ
ደማስቆ
የአርሞንዔም ተራራ
ፊንቄ
ታላቁ
ባሕር
ከነዓናውያን
የዮርዳኖስ ወንዝ
N
ፍልስጥኤማውያን
ኢየሩሳሌም
የጨው
ባሕር
0 10 20 30 40 50
ኪሎሜትር
ቤርሰባዕ
፯ኛ ካርታ
የሳኦል
መንግሥት


ቆጵሮስ
ታላቁ ባሕር
ፊንቄ
ሶርያ፡ አራም
የኤፍራጥስ ወንዝ
ደማስቆ
ሰማርያም
የዮርዳኖስ ወንዝ
ምድያን
ኢ.የሩሳሌም
የጨው ባሕር
ኬብሮን
ቤርሳቤዕ
ዓሞን
ሞአብ
ኤዶምያስ
ኤላት
የግብፅ ወንዝ
N
ኪሎሜትር
0 40 80 120
፯ኛ ካርታ
የዳዊትና የሰሎሞን
መንግሥት ግዛት

# የሰሎሞን መንግሥት መከፋፈል።

(በ፳ኛው ካርታ ላይ ተመልከቱ ።)

ሰሎሞን በሞተ ጊዜ (በ935 ዓመተ ዓለም) መንግሥቱ በአምስት ክፍሎች ተከፋፈለ፤ ይኸውም—

፩ኛ <u>ሶርያ (አራም)።</u> ከአርሞንዔም ተራራ በስተ ሰሜን እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ አንድ ግዛት ሆነ ። መናገሻው ከተማ ደማስቆ ነበር ።

፪ኛ <u>እስራኤል</u> ወይም «አሥሩ ነገዶች» ። ይህም መንግሥት በየሮብዓም በ935 ዓመተ ዓለም ተመሠረተ ። መናገሻው ከተማ ሰማርያ ሆነ ።

፫ኛ <u>ይሁዳ ።</u> ከእስራኤል አገር በስተ ደቡብ ነበር ። እርሱም የይሁዳንና የብንያምን ርስት ምናልባትም የስምዖን አካፋይ መሬት ሳይጠቀልል አልቀረም ። የእስራኤልንና የይሁዳን መንግሥታት የሚለየው ወሰን ከኢያሪኮና ከቤትኤል ደቡብ ነበረ ። ዋናው ከተማ ኢየሩሳሌም ነበረ ።

፬ኛ <u>ሞአብ ።</u> ይህ አገር ከጨው ባሕር በስተ ምሥራቅ የሚገኝ ነበር ።

፭ኛ <u>ኤዶምያስ (ኤዶም) ።</u> ይህም የሚገኘው ከጨው ባሕር በስተ ደቡብ ነበረ ።

ከ935 ዓመተ ዓለም ጀምሮ እስከ 842 ዓመተ ዓለም በእነዚህ መንግሥታት መካከል ብዙ ውጊያ ነበረ ።

# የምርኮ ዘመን ።


<u>የእስራኤል መውደቅ</u> (742 ዓመተ ዓለም እስከ 721 ዓመተ ዓለም) ።

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ዘመን የተነሣው የአሶር መንግሥት ነበር ። የመንግሥቱም መናገሻ ከተማው ነነዌ ነበር ። እርሱም አስቀድሞ ሶርያን በኋላም ትንሽ ቆይቶ እስራኤልን አሸነፈ ። ሰማርያም በ721 ዓመተ ዓለም ተያዘ ። በመጨረሻውም አሥሩ ነገዶች በምርኮኛነት ተወሰዱ (፪ኛ ነገሥ. ምዕ. ፲፯) ።

<u>የይሁዳ አገር መውደቅ</u> (721 ዓመተ ዓለም እስከ 586 ዓመተ ዓለም) ።

እስራኤል ከተሸነፈ በኋላ የይሁዳ መንግሥት ከአንድ መቶ ዓመታት ለሚበልጥ ዘመን ሳይያዝ ቆየ ። በዚህ በመቶ ዓመታት ውስጥ በይሁዳ አገር የተፈጸሙ ዋና ዋና ነገሮች የሚከተሉት ናቸው—

፩ኛ ንጉሥ ሕዝቅያስ የአገሩን ባዕድ አምልኮ ማስወገድና በሰናክሬብ ተከበባ የነበረችውን ኢየሩሳሌምን ከአሶር መንግሥት እጅ ማስለቀቅ (፪ኛ ዜና ምዕ. ፴


ታላቁ ባሕር
ሶርያ (አራም)
ደማስቆ
የአርሞንዔም ተራራ
ዳን
የዓረብ
ምድረ በዳ
ሰማርያ
እስራኤል
ኢያርኮ
ዓሞን
ኢየሩሳሌም
የጨው ባሕር
ሞአብ
N
0 20 40 60 80 100
ኪሎሜትር
ይሁዳ
ኤዶምያስ
ኤላት
፳ኛ
ካርታ
የሰሎሞን
መንግሥት
መከፋፈል

እስከ ምዕ. ፴፪)።

፪ኛ የንጉሥ ምናሴ በአሶራውያን መማረክና የእርሱም መመለስ (፪ኛ ዜና ፴፫፥ ፩—፳)።

፫ኛ ንጉሥ ዮስያስ አገሩን ለማሻሻል መሞከሩና በመጊዶን መሞቱ (፪ኛ ዜና ምዕ. ፴፬ና ፴፭፤ ፪ኛ ነገሥ. ፳፫፥ ፩—፴)።

፬ኛ የባቢሎን መንግሥት መነሣትና በኢዮአቂም መንግሥት ጊዜ የናቡከደናጾር የመጀመሪያው የይሁዳን አገር መውረር (606 ዓመተ ዓለም)። ከዚህ ዘመን ጀምሮ የይሁዳ አገር የባቢሎን ቅኝ ግዛት ሆነች። ሰባው የምርኮ ዓመታት የተባለው ዘመን መቆጠር የተጀመረው ከዚህ ጊዜ ወዲህ ነው።

፭ኛ የጼድቅያስ የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ በናቡከደነጾር ላይ ማመፅ፤ የመንግሥቱ መፍረስ፤ ይሁዳ በባቢሎን መንግሥት መማረክ (586 ዓመተ ዓለም)። የናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን ፈጽሞ ማጥፋትና የይሁዳም መንግሥት መደምሰስ (፪ኛ ነገሥ. ምዕ. ፳፭)።

# የአሕዛብ የምሥራቅ መንግሥታት።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ከአብርሃም እስከ ዕዝራ ድረስ ባሉት ዘመናት ውስጥ አራት ትልልቅ የምሥራቅ መንግሥታት ተከታትለው ተነሥተው ስለነበረ በየተራ አንዱ መንግሥት ሲወድቅ ሌላው ሲነሣ የፈጁት ዘመን ከ1,500 ዓመታት ይበልጣል። እነዚህም መንግሥታት እንደቅደም ተከተላቸው ቀጥሎ ተዘርዝረዋል።

፩ኛ <u>የጥንቱ ባቢሎን መንግሥት</u>። ይህ መንግሥት ከ2,000 እስከ 1,120 ዓመተ ዓለም ድረስ ቆየ። ይህም ጊዜ አብርሃም፤ ያዕቆብና ሙሴ የኖሩበት ዘመን ነበር።

፪ኛ <u>የአሶር መንግሥት</u>። ይህ መንግሥት ከ1,120 እስከ 606 ዓመተ ዓለም ድረስ ቆየ። ይህም ጊዜ ሙሴ፤ ዳዊትና ዮስያስ የኖሩበት ዘመን ነበር።

፫ኛ <u>የባቢሎን (የከለዳውያን) መንግሥት</u>። ይህ መንግሥት ከ606 እስከ 536 ዓመተ ዓለም ድረስ ቆየ። ይህም ጊዜ አይሁዶች የተማረኩበት ዘመን ነበር።

፬ኛ <u>የፋርስ መንግሥት</u>። ይህ መንግሥት ከ536 እስከ 330 ዓመተ ዓለም ድረስ ቆየ። ይህም ጊዜ ዕዝራና ነህምያ የኖሩበት ዘመን ነበር።

# የሮማ መንግሥት ።

(በ፱ኛው ካርታ ላይ ተመልከቱ ።)

በሚልክያስ ዘመን የብሉይ ኪዳን ታሪክ በሚፈጸምበት ጊዜ በሥልጣን ላይ የነበረው የአሕዛብ መንግሥት ፋርስ ነበር ። በኋላም በኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን ይኸውም የአዲስ ኪዳን ታሪክ በተጀመረበት ጊዜ የሮማ መንግሥት ዓለምን ይገዛ ነበር ። ከብሉይ ኪዳን ታሪክ መጨረሻ ጀምሮ ክርስቶስ እስከተወለደበት ድረስ በነበረው በ400 ዓመታት ውስጥ የሆነውን ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምረንም ። ነገር ግን በዓለም ታሪክ ውስጥ እንደምናነበው የግሪክ መሪ የነበረ ትልቁ እስክንድር የፋርስን ሰዎች ያሸነፈበትና በኋላም የግሪክ መንግሥት በፈንታው ወድቆ ሥልጣኑን የሮማ መንግሥት የወረሰበት ዘመን ነበር ። የሮማ መንግሥት ታላቅ ሆኖ እንዴት እንደተስፋፋ በካርታው ላይ ይታያል ።

